ምዕራፍ 14-19

2. ለሌሎቹ ነገዶች ርስት መሰጠቱ ።

ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ስድስት ምዕራፎች ለሌሎቹ ነገዶች የርስት ማከፋፈል እንደተደረገ እናያለን ። ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ተኩል ነገዶች ርስት የተሰጠው በሙሴ አማካይነት ነበረ፤ ከዚህ በኋላ ላሉት ግን ርስት የተከፋፈለው በካህኑ በአልዓዛርና በኢያሱ አማካይነት ነው ። ርስት እንዲከፋፈል የተደረገው በነ ገዶቹ ምርጫ ሳይሆን በዕጣ ነበር ፤ 14፡2 ። ዕጣ ፤ በሚከፋፈሉ ሰዎች መሃከል ማጉረምረም እንዳይኖር የሚያደርግ በዚያን ጊዜ የተለመደ አሠራር ነበር ፤ ምሳ.16፡33 ። ቀደም ተብሎ እንደተ ገለጸው የሌዊ ነገድ የራሳቸው የሆነ ርስት አላገኙም ፤ 14፡3 ።

ከዚህ በኋላ ያሉት ምዕራፎች የእስራኤል ነገዶች በምን ዓይነት ሁኔታ ርስት እንደተከፋፈሉ ያሳያሉ ።

ሀ/ ለካሌብ የተሰጠው ርስት 14፡6-15

ካሌብ ሙሴ በሰላይነት ልኳቸው ከነበሩት አንዱ ሲሆን ፤ ዘኍ. 13፡6 ፤ የሚኖረውም በይሁዳ ሰዎች መሃከል ነበር ። ተል ከው ከነበሩት ሰላዮች መሃከል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ድል ይሰጣል ብለው የተናገሩ እርሱና ኢያሱ ብቻ ነበሩ ። ይህ ሰው ሙሴን የእግዚአብሔር ባርያ ወይም የአምላክ ሰው እያለ ሲጠራው እንመለከታለን ።

ካሌብ ለሰላይነት የተላከው በአርባ ዓመቱ ነበር ። ከስለላ በተመለሰበት ጊዜ ርስት የሚሰጠው መሆኑን የሚገልጽ ተስፋ ከሙሴ ተሰጠው ። አሁን በዚህ ተስፋ መሠረት ርስት እንዲሰ ጠው ለመጠየቅ ተነሣ ። ይህ ተስፋ እንዲፈጸምለት የጠየቀው

በሰማንያ አምስት ዓመቱ ነው ። በዚህ ዕድሜው በአርባ ዓመት የነበረው ጉልበቱ አልደከመም ነበር ።

ሙሴ ‘‘እግርህ የረገጠው ምድር ለአንተና ለልጆችህ ለዘ ለዓለም በእርግጥ ርስት ይሆናል ’’ ብሎ በማለለት መሠረት ካ ሌብ ተራራማ የሆነውንና የዔናቃውያን ታላላቆች የያዟቸው የተመሸጉ ከተሞች የሚገኙባቸውን ከተሞች ርስት አድርጐአን ዲሰጠው ኢያሱን ጠየቀ ። አ.ያሱም የካሌብን ጥያቄ ተቀብሎ ኬብሮንን ለካሌብ ርስት አድርጎ ሰጠው ። ከዚያም በኋላ በኬ ብሮን ምድር የነበረው ውጊያ አከተመ ፤ ቁጥር15 ።

ከግብጽ ከወጡት እስራኤላውያን መሃከል ተስፋዬቱ ም ድር መድረስ የቻሉት ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ ፤ ካሌብን ለዚህ ታላቅ ዕድል ያበቃው አምላኩን እግዚአብሔርን ፈጽሞ መከ ተሉ ነበር ፤ ቁጥር 9 ። ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ፍጹም በ ሆነ መንገድ ቢከተሉት ከእግዚአብሔር ታላቅ በረከት የሚያ ገኙ መሆናቸውን የካሌብ ታሪክ ያሳያል ። ለብዙዎች ክርስትና በእሑድ ቀን ቤተክርስቲያን መምጣት ብቻ ይመስላቸዋል ። እግዚአብሔር ግን ከአማኞች የሚፈልገው የእሑድ ክርስትናን ሳይሆን ፍጹም በሆነ መንገድ እርሱን መከተልን ነው ።

ካሌብ በሽምግልናው ዘመን እንኳን ጉልበቱ ያልደነዘዘ ፣ ዓይኑ ያልፈዘዘ ሰው ነበር ። ስለዚህም በግዙፍነታቸው አስፈሪ የሆኑትን የዔናቅን ሰዎች በአምላኬ ኃይል እቋቋማለሁ በሚል ድፍረት እነርሱ ያሉበት ተራራማ አካባቢ ርስት ተደርጎ እንዲ ሰጠው ጠየቀ ። ይህ የካሌብ እምነት በአምላኩ የሚታመንሰው ‘‘አምላኬ ያሳፍረኛል’’ የሚል ጥርጣሬ እንደማይኖረው ያሳየ ናል ። ካሌብ በሕይወቱ ያለው የአምላኩ አሸናፊነት በርሱ ዕድ ሜ እንደማይወሰን ተረዳ ። እንደ ኢያሱና እንደ ካሌብ እግዚአ ብሔርን በመታዘዝና በታማኝነት እንኑር ።

ምዕራፍ 15

ለ/ ለይሁዳ ነገድ የተሰጠው ርስት ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ባለፈው ምዕራፍ ርስትን እንደተቀበለ የተነገረለት የካሌብም ታሪክ ቀጥሏል ። ርስቱን በእጁ ካገባ በኋላ ዝም ብሎ አልተቀመጠም ። በዚያ ምድር የነበሩትን የሜናቅ ሰዎች በሙሉ አስለቀቃቸው ። በአካባቢው የነበሩትን ጎበ ዛዝት በማነሣሣት የሜናቅን ሰዎች እንዲያባርሩ አደረገ ፤ ቁጥር 13-19 ። የተሰጠውን የተስፋ ምድር በእጁ እስኪያገባ አላረፈም።

ሌሎቹ የይሁዳ ነገድ ሰዎች ግን የካሌብን አርአያነት አል ተከተሉም ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከተው የተስዱቱን ምድር ሙሉ በሙሉ ሊይዙ ሲገባቸው ጦርነትን በመሰልቸት ከጠላቶቻቸው ጋር ተስማምተው እንደተቀመጡ ነው ። ለይ ሁዳ ነገድ ሰዎች የተሰጠውን ርስት ከካርታ መመልከት ይቻ ላል ።

የኢየሩሳሌም ከተማ የምትገኘው ለይሁዳ ነገድ በተሰ ጠው ርስት ክልል ውስጥ ነው ። ሆኖም እስከ ዳዊት ዘመን ድ ረስ ሙሉ በሙሉ በእጃቸው አልገባችም ነበር ፤ 2ኛ ሳሙ. 5፡ 6-7 ። ርስት ተደርጎ የተሰጣቸው ግን እስከ ሜዲተራኒያን (ታላ ቁ) ባሕር ድረስ ያለውን አካባቢ ይጠቀልል ነበር ። ሆኖም እግ ዚአብሔር ተስፋ አድርጎ የሰጣቸውን ርስት በእጃቸው ለማግ ባት እስከመጨረሻ ስለአልጸኑ በዳዊት ዘመን እንኳ ፍልስጥኤ ማውያን ያስቸግሩአቸው ነበር ። እንዲያውም ኢያቡሳውያን በ ኢየሩሳሌም ተቀምጠው የነበሩ መሆናቸው በቁጥር 63 ውስጥ ተገልጿል ።

ከቁጥር 20 ጀምሮ ባሉት ጥቅሶች የይሁዳ ልጆች ርስት ሁኔታ በሚገባ ተብራርቷል ። በዚሁም መሠረት 123 ስሞች ተዘርዝረዋል ፤ ከስሞቹም መሃከል 112 ያህሉ የከተማ ስሞች ናቸው ። በዚሁ ዝርዝር ውስጥ አቃሮን ፣ አሽዶድና ጋዛ የተባሉት የፍልስጥኤማውያን ከተሞች ተጠቅሰዋል ፤ ቁ.45-47 ።

በመጽሐፈ ኢያሱና በመጽሐፈ መሳፍንት የሚገኘው ታሪክ በአጠቃላይ የሚገልጸው እስራኤላውያን በዚህ ተስፋ መቁረጣቸው ምክንያት የተስፋዪቱን ምድር ሙሉ በሙሉ ለመያዝ አለመቻላቸውን ነው ። እግዚአብሔርን በማማሸ መታዘዝ ትርፉ ይኸው ነው ። ስለዚህ አምላካችንን ሙሉ በሙሉ ልንታዘዘው ያሻናል ።

ምዕራፍ 16 ና 17

ሐ ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገዶች የተሰጠው ርስት ።

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ለሁለቱ ነገዶች ስለተሰጠው ርስት ይናገራሉ ። በመጀመሪያ ለኤፍሬም ነገድ ስለተሰጠው ርስት የተነገረውን ዝርዝር እንመለከታለን ።

በ16፡5-9 እንደምናየው ለኤፍሬም ነገድ ሰዎች ሰፋ ያለ ርስት ተሰጥቶአቸው ነበር ። ቢሆንም በተሰጣቸው ርስት የነበሩትን ከነዓናውያን አላሳደዱም ነበር ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ ። ከጊዜ በኋላ ግን እነዚህ ከነዓናውያን እነርሱን ወደ ጣዖት አምልኮ እንዲያዘነብሉ አደረጓቸው ።

በ17፡1-2 እንደተገለጸው ደግሞ ከዮርዳኖስ ማዶ በስተ ምሥራቅ በኩል ያለው አካባቢ ለምናሴ ነገድ ሰዎች ተሰጠ ።ከዚ

ሁ ነገድ ለሆኑት ለሰለጰዓድ ሴቶች ልጆችም ሙሴ በዘኍል.27፡6-7 በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በወንድሞቻቸው መሃከል ርስት ተሰጣቸው ፤ 17፡3-6 ። በቁ.7-13 እንደተገለጸው ደግሞ ለግማሾቹ የምናሴ ነገድ ሰዎች ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በኩል ያለው ርስት ተሰጣቸው ። ሆኖም የዚህ ነገድ ሰዎችም ከነዓናውያንን ከርስታቸው እንዲወጡ አላደረጉም ፤ ቁ.12-13 ። እንዲያውም የኤፍሬም ነገድ ሰዎች እንዳደረጉት እነሱም የከነዓንን ሰዎች ያለ ዋጋ ያሠሩአቸው ጀመር ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚሁ የዮሴፍ ልጆች ወደ ኢያሱ ቀረቡና የተሰጠን ርስት በቂያችን አይደለም የሚል አቤቱታ አቀረቡ ፤ ቁ.14 ። ኢያሱ ግን በፈርዛውያን የተያዙትን አካባቢዎች አስለቅቀው እንዲይዙ ነገራቸው ። ቢሆንም እነርሱ ከነዓናውያንን አንችላቸውም የሚል ምክንያት አቀረቡ እንጂ ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም ። አሁንም ኢያሱ ለነዚህ ሰዎች የጥበብ መልስ ሰጣቸው እንጂ ተጨማሪ ርስት ሊሰጣቸው አልፈለገም ። በኢያሱ መልስ መሠረትም በውጊያ ተጨማሪ ሥፍራ ለማግኘት መታገል አለባቸው እንጂ እጃቸውን አጣምረው መጠበቅ የለባቸውም ። ምንም ሳይሠሩ ማግኘትን ለሚፈልጉ ሰዎች የኢያሱ መልስ ጥሩ ትምህርት ይሰጣል ። እንደ ዮሴፍ ልጆች ሁል ጊዜ ሲያጉረመርሙና ሲያማርሩ የሚገኙ ሰዎች ሥራ መሥራትንና ተዋግቶ ድል ማግኘትን የማይፈልጉ ናቸው ። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ለሥራ ቢዘጋጁ ሰፊ የሆነ የሥራ መስክ ሊያገኙ ይችላሉ ።

ምዕራፍ 18 እና 19

መ/ሰሌሎቹ ነገዶች የተሰጠው ርስት ።

የእስራኤል ልጆች በሴሎ ተሰብስበው የመገናኛውን ድን ኳን እንደተከሉ ከምዕራፍ አሥራ ስምንት መጀመሪያ ላይ እን ረዳለን ። የጌታም ታቦት በዚሁ ድንኳን ውስጥ ነበረ ። ንጉሥ ዳዊት ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንዲመጣ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ (2 ሳሙ.6፡12) እስራኤላውያን ይሰበሰቡ የነበረው በዚሁ በሴሎ ነበር ።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በተስፋዱቱ ምድር በነበ ሩት ጠላቶቻቸው ላይ ታላቅ ድል ሰጥቶአቸው ነበር ፤ ቢሆንም ከአሥራ ሁለቱ ነገዶች ሰባቱ ገና ርስታቸውን አላገኙም ነበር ። ስለዚህ ኢያሱ ከየነገዱ ሦስት ሰዎች ተመርጠው መጥተው ለነ ዚህ ነገዶች ርስት እንዲያከፋፍሉ አደረገ ። የይሁዳ ፣ የኤፍሬ ምና የምናሴ ነገዶች ቀደም ሲል ርስት ተሰጥቶአቸው የነበረ ሲ ሆን የሌዊ ነገድ ሰዎች ግን ምንም ዓይነት ርስት እንዳይሰጣቸ ው ተደርጎ ነበር ። ኢያሱ ከሰባቱ ነገዶች የተመረጡትን ሃያ አ ንድ ሰዎች ለየነገዶቻቸው የሚያከፋፍሏቸውን ከተሞች ፣ ወን ዞችና ተራራዎች ስሞች በሙሉ በመጽሐፍ ጽፈው እንዲያቀ ርቡ አዘዛቸው ። በትእዛዙ መሠረት ጽፈው ባቀረቡበት ወቅ ትም ለሰባቱ ነገዶች ዕጣ ጥሎ በዕጣቸው መሠረት ርስትን አከ ፋፈላቸው ፤ 18፡2-10 ።

በወጣውም ዕጣ መሠረት ሰባቱ ነገዶች ከዚህ ቀጥሎ በቀ ረበው ዝርዝር መሠረት ርስት አገኙ ።

1. <u>የብንያም ነገድ</u> ፡- ይህ ነገድ ዕጣ የወጣለት በይሁዳ ልጆችና

በዮሴፍ ልጆች መሃከል ያለውን ርስት እንዲያገኝ ነበር ፤18፡ 11-28 ። በዚህም መሠረት የኢያቡስ ወይም የኢየሩሳሌም ከተማ ከፊሉ የብንያም ነገድ ድርሻ ሆነ ። ቢሆንም የይሁዳም ሆነ የብንያም ነገድ ሰዎች ኢያቡሳውያን ከመሃከላቸው እንዲወጡ አላደረጉም ፤ 15፡63 ፤ መሳፍ.1፡21 ።

2. <u>የስምዖን ነገድ</u> ፡- የይሁዳ ነገድ ሰዎች ከሚያስፈልጋቸው በላይ የሆነ ርስት ይዘው ስለነበረ በስተደቡብ በኩል ያለው ምድር ለስምዖን ነገድ ሰዎች ተሰጠ ፤ 19፡1-9 ። የይሁዳ ነገድ ሰዎች ይዘዋቸው የነበሩት ሽማዕ ፣ ሞላዳ ፣ ቤርሳቤህ ፣ሔርማ ፣ ጺቅላግና ዓይን የተባሉት ከተሞች ለስምዖን ነገድ ሰዎች ተሰጡ ፤ 15፡26-32 ።
3. <u>የዛብሎን ነገድ</u> ፡- ለዚህ ነገድ የተሰጠው ርስት የሚገኘው ለምናሴ ነገድ ከተሰጠው ርስት በስተ ሰሜን በኩል ሲሆን በውስጡም አሥራ ሁለት ከተሞች ነበሩበት ፤ 19፡10-16 ።
4. <u>የይሳኮር ነገድ</u> ፡- ይህ ነገድ የተሰጠው ርስት በውስጡ አሥራ ስድስት ከተሞች የነበሩበት ሲሆን የሚገኘውም ከምናሴ ነገድ ርስት በስተ ሰሜን በዛብሎን ነገድ ርስትና በዮርዳኖስ ወንዝ መሃከል ነበር ፤ 19፡17-23 ።
5. <u>የአሴር ነገድ</u> ፡- ከዛብሎን ነገድ ርስት በስተ ሰሜን በኩል እስከ ታላቁ (ሜዲተራኒያን) ባሕር ድረስ ያለውን አካባቢ የሚጠቀልል ሃያ ሁለት ከተሞች ያሉት ርስት ተሰጠው ፤ 19፡24-31 ።
6. <u>የንፍታሌም ነገድ</u>፡- ለዚህ ነገድ የተሰጠው ርስት የሚገኘው ደግሞ ከአሴር ነገድ ርስት በስተ ምዕራብ ከዛብሎንና ከይሳኮር ነገዶች ርስት በስተሰሜን በኩል ሲሆን ፣ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ የሚደርስ ከመሆኑም በላይ አሥራ ዘጠኝ

ከተሞችን ያጠቃልል ነበር ፤ ም. 19፡32-39 ።

በቁጥር 34 ይሁዳ የሚለው ቃል የተጠቀሰው ነገዱን ለማመልከት ሳይሆን የነገዱን ርስት ለማመልከት ነው ፤ ይህ ርስት ከዮርዳኖስ ወንዝ አንስቶ የገሊላን ባሕር ደቡባዊ ክፍል ይጠቀልላል ።

7. <u>የዳን ነገድ</u> ፡- ይህ ነገድ የተሰጠው ርስት የሚገኘው በይሁዳና በኤፍሬም ነገዶች ርስት መሃከል ፣ ከብንያም ነገድ ሰዎች ርስት በስተ ምዕራብ በኩል ነው ። ለዚህ ነገድ የተሰጡት ከተሞች ይገኙ የነበረው በታላቁ ባሕር አካባቢ በመሆኑ በዚያው አጠገብ ሰፍረው የነበሩትን ፍልስጥኤማውያንን የዚህ ነገድ ሰዎች ማስወጣት አልቻሉም ።

ከዳን ነገድ ሰዎች ጥቂቶቹ የያዙት ቦታ ስለአልበቃቸው ከንፍታሌም በስተ ሰሜን በኩል ወደምትገኘው ወደ ሌሻም ከተማ ሄደው ድል አድርገው ያዙአት ። ከዚያም የከተማዪቱን ስም በአባታቸው በዳን ሰየሙአት ፤ 19፡47 ፤ መሳፍንት 18፡7 ፣ 27-29 ።

በመጨረሻም ኢያሱ በኤፍሬም ምድር ውስጥ የምትገኘውን ተምናሴራ የምትባለውን ከተማ ለራሱ ወሰደ ይህች ከተማ ለራሱ እንድትሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበረ ሕዝቡ በዚህ ተስማሙ ። ኢያሱም በዚህች ከተማ ደስ ተሰኘ ፤ ቁ. 49-50 ። ሰዎች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ፈቃድ ሲያውቁ ከእግዚአብሔር ጋር በደስታ መኖር ይችላሉ።

ምዕራፍ 20

ሠ የመማጸኛ ከተሞች

ለሁሉም ነገዶች ርስት ከተከፋፈለ በኋላ የቀረው አንድ ሥራ ደግሞ ስድስት የመማጸኛ ከተሞችን ማዘጋጀት ነው ። እያ ወቀ ሌላውን ሰው የሚገድል ሰው እንዲገደል እግዚአብሔር አዟል ። ነገር ግን ባለማወቅ ሌላውን የሚገድል ሰው ወደ መማ ጸኛ ከተሞች እንዲሸሽ ተፈቅዶለታል ፤ ዘጸአት 21 ፡ 12-14 ። ሙሴ የመማጸኛ ከተሞችን እንዲሠራ የታዘዘው ለዚሁ ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ነበር፡ዘኍ. 35፡9-34።በዘዳግም 19፡2-13 ሙሴ የእስራኤልን ሰዎች ይህንን ትእዛዝ እንዲፈጽሙ አስ ገንዝቦአቸዋል ። በ20፡1-6 ደግሞ ጌታ ኢያሱን እነዚህን የመ ማጸኛ ከተሞች እንዲሠራ እንደነገረው እንመለከታለን ።

ባለማወቅ ነፍስ የገደለ ሰው ወደነዚህ ከተሞች መሸሽ ይችላል ፤ የተገደለውም ሰው ወንድም በገዳዩ ላይ የበቀል እርም ጃ መውሰድ አይችልም ። ገዳዩም ሰው ጉዳዩ ወደ ፈራጆች ፊት ቀርቦ እስኪወሰንለት ወይም ነፍስ በገደለበት ጊዜ በሕይወት የነበረው ሊቀ ካህን እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ከዚያች ከተማ አይወጣም ነበር ። ጉዳዩ ከተወሰነለት ወይም ሊቀ ካህኑ ከሞተ ግን ከዚያች ከመማጸኛ ከተማ ወጥቶ ወደ ቤቱና ዘመዶቹ መሄድ ይችል ነበር ።

በዚሁ መሠረት እስራኤላውያን በስተሰሜን ቃዴስን ፣ በመካከል ሴኬምን ፣ በስተደቡብ ኬብሮንን ፣ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ቦሶርን ፣ ራሞትንና ገላንን የመማጸኛ ከተሞች እንዲ ሆኑ አደረጉ ። ምንም እነዚህ ስድስት ከተሞች የመማጸኛ ከተ

ግ ቢደረጉም በታሪካቸው ውስጥ ማንም ነፍሱን ለማዳን ወደነ ዚህ ከተሞች እንደሸሸ አናነብም ። አንዳንዶች ግን በዚህ ፋንታ ወደ መገናኛው ድንኳን ሲሸሹ እንደነበረ ተጽፏል ፤ 1 ነገ. 2፣ 28 ።

የመማጸኛ ከተሞች የክርስቶስ ምሳሌ ናቸው ። ኃጢአ አተኞች እንደመሆናችን ሕይወታችንን ለማዳን መሮጥ የም ንችለው ወደ ክርስቶስ ብቻ ነው ። እስራኤላውያን የመማ ጸኛ ከተሞችን ጥቅምና አገልግሎት ቢያውቁም እንዳልተጠቀ ሙባቸው ከላይ ተመልክተናል ። ዛሬም ብዙዎች የክርስቶስን ማዳንና የራሳቸውን ኃጢአተኝነት ቢያውቁም ወደ ክርስቶስ አይመጡም ። ውጤታቸውም ጥፋት ይሆናል ።

ረ/ <u>የሌዋውያን ከተሞች</u>

በዘኁል. 35 ፡ 1-8ና በኢያሱ 21 ፡ 1 - 3 እንደምንመለከ ቀው እግዚአብሔር ለሌዋውያን የመሬት ድርሻ የሆነ ርስት ሳይሆን ከተሞች እንዲሰጧቸው አዞ ነበር ፤ በተጨማሪም ከሚ ሰጧቸው ከተሞች ጋር ለከብቶቻቸው ማሰማሪያ የሚሆን አነስ ተኛ ሥፍራ እንዲፈቀድላቸው አዞ ነበር ። በዚሁም መሠረት ለሌሎቹ ነገዶች ርስት ተሰጥቶ ከአበቃ በኋላ የሌዊ ነገድ ሰዎች ወደ እስራኤል ሕዝብ አለቆች ፊት ቀረቡ ፤

ሌዊ ፡ ቀዓት ፡ ጌድሶንና ሜራሪ የሚባሉ ሦስት ልጆች ነበ ሩት ። ካህኑ አሮንም የሌዊ ልጅ የቀዓት ተወላጅ ነበር ። የአሮን ልጆች አሥራ ሦስት ከተሞች ተሰጧቸው ፤ ለሌሎቹ የቀዓት ልጆች አሥር ከተሞች ፡ ለጌድሶን ልጆች አሥራ ሦስት ከተ ሞች ፡ ለሜራሪ ልጆች አሥራ ሁለት ከተሞች በድምሩ አርባ ስምንት ከተሞች ተሰጧቸው ፤ 21 ፡ 4 - 8 ።

በ19 ፡ 1 እንደተመለከትነው ከይሁዳ ነገድ ርስት ከፊሉ በብንያም ነገድ ሰዎች እጅ ገብቶ ነበር ፤ እነዚህ ሁለት ነገዶች በአንድነት ሆነው ፡ በ15 ፡ 13 እንደተገገጸው የካሌብ ድርሻ የሆ ነችውን የኬብሮንን ከተማ ጨምረው በድምሩ ዘጠኝ ከተሞች ን ለሌዋውያን ሰጡአቸው ። ካሌብ ከከተማው ዙሪያ የነበሩትን መንደሮች ለራሱ ወሰዶ የኬብሮንን ከተማ ከዳቤር ከተማ ጭም ር ለአሮን ልጆች ሰጣቸው ፤ 15፡15 ፤ 21፡15 ።

የብንያም ነገድ ሰዎች አራት ከተሞችን ለአሮን ልጆች ሰጡ ፤ ቁ. 17 - 18 ። የተቀሩት የቀዓት ልጆች ከኤፍሬም ነገድ ሰዎች አራት ከተሞችን ፡ ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ሁለት ከተሞ ችን በጠቅላላ አሥር ከተማዎች አገኙ ፤ 21 ፡ 20 - 26 ።

የጌድሶን ልጆች ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በኩል ከሚኖ ሩት ከግማሽቹ የምናሴ ነገድ ሰዎች የመማጸኛ ከተማ የሆነች ውን የጎላንን ከተማ ፡ አንድ ሌላ ከተማ ፡ ከይሳኮር ነገድ ሰዎች አራት ከተሞች ፡ ከአሶር ነገድ ሰዎች አራት ከተሞች ፡ ከንፍታ ሌም ነገድ ሰዎች የመማጸኛ ከተማ የሆነችውን ቃዴስንና ሌሎ ች ሁለት ከተሞችን በድምሩ አሥራ ሦስት ከተሞች አገኙ ።

የሜራሪ ልጆች ደግሞ ከዛብሎን ነገድ ሰዎች አራት ከተ ሞችን ፡ ከሮቤል ነገድ ሰዎች አራት ከተሞችን ፡ ከጋድ ነገድ ሰዎች አራት ከተሞችን በድምሩ አሥራ ሁለት ከተሞች ተሰጧ ቸው ፤ ራሞትና ኢያዜር የተባሉት ሁለቱ የመማጸኛ ከተሞች ከነዚህ አሥራ ሁለት ከተሞች ሁለቱ ናቸው ፤ 20 ፡ 38 - 39 ።

ለሌዊ ሦስት ልጆች ተወላጆች ከከብት ማሰማሪያ ሥፍራ ዎች ጋር የተሰጡት ከተሞች ብዛት ከስድስቱ የመማጸኛ ከተ ሞች ሌላ አርባ ሁለት ይደርስ ነበር ።

ይህ ታሪክ እግዚአብሔር የገባውን ቃል የሚፈጽም አም

ላክ መሆኑን ያስተምረናል ። ሌዋውያን እግዚአብሔር ለተለየ ሥራ የመረጣቸው ወገኖች በመሆናቸው ርስት አልተሰጣቸው ም። ቢሆንም ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ መኖሪያ የሚሆኑ ከተሞች ተሰጥተዋቸው ነበር ። በተጨማሪም እስራኤላውያን ከሚያገኙት ገቢ በሚሰጡት አሥራት እንዲተዳደሩ ተደርገ ዋል ፣ ዘኁ. 18፡21 ።

እግዚአብሔር ሌዋውያንንና ካህናትን የመረጠው ከእርሱ የተሰጠውን ሕግ ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ ነው ፣ ዘሌዋ. 10፡11፣ 2ዜና. 35፡3 ፣ ነህ. 8፡9 ። ከዚህ ጋር ማስታወስ የሚገባን እግዚ አብሔር ለዚህ ዓላማው ሌዋውያን በሌሎቹ የእስራኤል ነገዶች መሃከል እንዲኖሩ ማድረጉን ነው ። ለዚሁም ጉዳይ የይሁዳና የስምዖን ነገድ ሰዎች ዘጠኝ ከተሞችን ፣ የንፍታሌም ነገድ ሰዎች ሦስት ከተሞችን ሲሰጡ የተቀሩት ነገዶች ግን አራት አራት ከተሞችን ሰጡ ።

ከላይ በተመለከትነው መንገድ እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ በረከትን አሟላላቸው ። ምዕራፉ እግ ዚአብሔር የተናገረውን ቃል አንድም ሳያስቀር እንደፈጸመ በማረጋገጥ ያበቃል ፣ ቁ. 45 ፣ 11፡23 ። እግዚአብሔር የተናገረ ውን ቃል አንዳችም ሳያስቀር የሚፈጽም አምላክ መሆኑን በእር ግጥ እንመን ።

ምዕራፍ 22

ሰ/ ሁለት ተኩሉ ነገዶች ወደ ርስታቸው መመለሳቸው

ከመጀመሪያው የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆንም የሁለት ተኩል ነገዶች ሰዎች ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው መሬት

ርስት እንዲሆን ተሰጥታቸው ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ቀርተው ነበር። የእነዚህ ነገዶች ሰዎች ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በኩል ያለው ፣ ለሌሎቹ ነገዶች ርስት ተደርጎ የሚሰጠው መሬት ነፃ እስኪሚ ወጣበት ጊዜ ድረስ በጦርነቱ ለመሳተፍ ቃል ገብተው ነበር ፤ 1፡16 ። በዚህም መሠረት ከእነርሱ መሃከል አርባ ሺህ ያህሉ ከጠላት ጋር በሚደረገው ውጊያ ወገኖቻቸውን ለመርዳት ከሌሎቹ ነገዶች ጋር ሆነው ዮርዳኖስን ተሻግረው ነበር ፤ 4፡13 ።

አሁን ውጊያ አብቅቷል ፤ ጦርነቱም ተፈጽሟል ። እነዚህ ሰዎች ወደ ርስታቸው መመለስ አለባቸው ። ስለዚህም ኢያሱ እኒህን ሰዎች ስለአደረጉት ነገር ሁሉ አመሰገናቸው ። ወደ ርስታቸውም ተመልሰው እንዲኖሩ ነገራቸው ። በዚያም አምላክን ከመከተል እንዳይመለሱ ከመከራቸው በኋላ አሰናበታቸው ። በዚህም ወቅት የባረካቸው መሆኑ ተገልጿል ፤ 22፡1 - 6 ።

ኢያሱ በዚህ ወቅት ለነዚህ ሰዎች ብዙ ባለጠግነት ሰጣቸው ። ወደ ርስታቸውም ሲመለሱ ያገኙትን ትሩፋት ለሌሎች እንዲያካፍሉ ነገራቸው ፤ 22፡7 - 9 ፤ እና 1 ሳሙ . 3 ፤ 24 ።

ከዚህ በኋላ እነዚህ የሁለት ተኩል ነገዶች ሰዎች ወደ ርስታቸው ለመመለስ ጉዞ ጀመሩ ። የዮርዳኖስን ወንዝ ከመሻገራቸውም በፊት ታላቅ መሠዊያ ሠሩ ። በአካባቢው የነበሩት ሌሎቹ የእስራኤል ሰዎች ይህንን ሲሰሙ በጣም ተቆጡ ፤ ሥራቸውንም ሊያስቆሙአቸው መጡ ፤ 22፡10 - 12 ።

ከእስራኤል ነገዶች ተልከው ወደነዚህ ሁለት ተኩል ነገዶች የመጡት ካህኑ ፊንሐስና ፤ የየነገዱ አለቆች ነበሩ ፤ 22፡13 - 14። መልእክተኞቹም ለሁለት ተኩሉ ነገዶች ሌላ መሠዊያ መሥራታቸው በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ መሆኑን ፤ እግዚአብሔርን ከመከተል ወደኋላ መመለስ መሆኑንና በዚህም የተነሣ የእግዚ

አብሔር ቁጣ በእስራኤል ሕዝብ ላይ እንደሚመጣ ገለጹላቸው። ይህ ድርጊታቸው የእግዚአብሔርን መቅሠፍት የሚያመጣ መሆኑን ብዔል ፌጎርን በተከተሉት እስራኤላውያን ላይ የመጣውን ቁጣና ፣ የአካን ኃጢአት ያስከተለውን ውጤት ታሪኮች በመግለጽ አስረዱአቸው ፤ ዘኍል. 25 ፡3፤ ኢያሱ 7 ። እነርሱ የሚሠሩትም ተመሳሳይ ኃጢአት መሆኑን ገለጹላቸው ። በተጨማሪም ደግሞ ፍላጐት ካላቸው በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ካሉት ከሌሎቹ ወገኖቻቸው ጋር አብረው መኖር የሚችሉ መሆኑን ነገሯቸው ።

ሁለት ተኩሉ ነገዶች ግን ከእስራኤል አለቆች የተሰነዘረው ትክክል አለመሆኑን የሚያስረዳ መልስ ሰጡ ፤ 22፡21-29 ። መሠዊያውን የሠሩት በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ ፣ እርሱን ከመከተል ወደ ኋላ ለመመለስ ሳይሆን ሌሎቹ ነገዶች የእነርሱን ከእስራኤል ወገን መሆን እንዲያስታውሱበት መሆኑን አስረዷቸው ። የሰጡትም መልስ በካህኑ ባፌንሐስና በአሥሩ ነገዶች አለቆች ዘንድ አጥጋቢ ሆኖ ተገኘ ። እነርሱም እግዚአብሔር ከሁለት ተኩሉ ነገዶች ጋር በመሆኑ ተማመኑ ። ወደ አሥሩ ነገዶችም ተመለሱና ሁኔታውን አስረዱ ፤22፡32 ። የእስራኤል ሰዎችም በሙሉ በነገሩ ደስ ተሰኙበት ።ሁለት ተኩሉም ነገዶች የሠሩትን መሠዊያ « ምስክር » ብለው ሰየሙት ፤ 22፡34 ።

ካዚህ ታሪክ ለአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖችና አብየተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑ ሦስት ታላላቅ ትምህርቶችን እናገኛለን ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።-

1. እስራኤላውያን የወንድሞቻቸውን አሳብ ሳይረዱ ፈረዱ ባቸው ። ወዲያውኑ ተነሥተው ሊዋጉአቸውና ሊያጠፉአቸው ተዘጋጅተው ነበር ። በኋላ ግን የወገኖቻቸውን አሳብ መልካምነት ተረዱ ። ይህ ሁኔታ የወንድሞቻችንን አሳብ

ሳናውቅ ልንፈርድባቸው የማይገባ መሆኑን ያስተምረናል ። በኋላ ልንጸጸትበት ስለምንችል ትዕግሥት ያስፈልገናል ።

2. ሁለት ተኩሉ ነገዶች ዓላማቸውንና አሳባቸውን ለሌሎቹ ወገኖቻቸው ገልጸው ቢሆንኖሮ ይህ ሁሉ አለመግባባት ባል ተፈጠረ ነበር ። በዚህ ዓይነቱ አሠራር ባለመጠቀማቸው ብዙ ምዕመናን ተመሳሳይ ችግሮች ገጥመዋቸዋል ። ጥቂት ሰዎች ብዙዎችን ሳያማክሩ አንዳንድ ሥራዎችን መጀመራቸው ውጤቱ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ብዙውን ጊዜ ችግሩ ከበድ ብሎ የሚታየው ምክንያቱን ጠይቆ ሳይረዱ ፍርድ ውስጥ በመግባት ነው ። የእግዚአብሔር ቃል "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ" ይላል ።

3. ሁለት ተኩሉ ነገዶች ከሌሎቹ ወገኖች ተገንጥለው ከዮርዳ ኖስ በስተ ምሥራቅ እንዲኖሩ እግዚአብሔር አልፈቀ ደም ። የእርሱ ፈቃድ አሥራ ሁለቱም ነገዶች ለራሳቸው ተገንጥለው መሠዊያ እንዲሠሩ አልነበረም ። በዚያ ፋንታ በዓመት ሦስት ጊዜ ሁሉም በአንድነት እንዲሰበሰቡ ነበር ። ይህም እንዲሆን ያቀደው የእስራኤል ነገዶች አን ድ መሆናቸው እንዲታወቅ ለማድረግ ነበር ።

ችግሩ ግን ሁለት ተኩል ነገዶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ አልተከተሉም ። በዚህ ፈንታ የራሳቸውን ምርጫ ተከተሉ ። የራሳቸውን ፈቃድ መፈጸም ፈለጉ ። ስለዚህም እግዚአብሔር ፈቀደላቸው ። ከዚህ በኋላ የራሳቸውን መ ሠዊያ እንዳሠሩ እናያለን ። ለዚህ ግን እግዚአብሔርን እንደ ጠየቁ በጭራሽ አልተጸፈም ።

በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ልንከተለው የሚገባን የኢየሱስንና የዳዊትን ምሳሌ ነው ። ጸሎታችን እንደ ኢየሱስ ጸሎት

ፈቃድህ ይሁን የሚል መሆን አለበት ። ኢየሱስ ወደ አባቱ ሲጸልይ የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን እንዳለ ከሉቃ. 22፡42 እንመለከታለን ። ስለዚህ ከራሳችን ፈቃድ ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናስቀድም ይገባ ናል ። ሁለት ተኩሉ ነገዶች በኑሮአቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳያውቁ አንድን ነገር መሥራት እንደቀጠሉ ከእግ ዚአብሔር መመሪያ ሳያገኙ መሠዊያ ከመሥራታቸው እን ማራለን ።

ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤትን ለመሥራት በተነሣበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተከተለ ። እግዚአብሔር ቤቱ እንዲሠራ የሚፈልግበት ጊዜ ያልደረሰ መሆኑን ሲረ ዳ ዝም ብሎ መቀመጥ ያለበት መሆኑን ተገነዘበ ፤ 2 ሳሙ. 7፡1-7 ። ጳውሎስ ለእስያ ሰዎች ወንጌል ለመስበክ ሲዘጋጅ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሌላ ቦታ ስለጠራው አሳቡን ለወጠ ፤ የሐዋ. 16፡6-9 ።

ልንሠራ ያቀድነው ሥራ ምንም መንፈሳዊና ቅዱስ ሥራ ቢሆን የእግዚአብሔር ን መመሪያ ልንከተል ያሻናል የሥጋን ጥበብ ከመከተል መቆጠብ ያስፈልገናል ።

ክፍል አምስት

ምዕራፍ 23 እና 24

ኢያሱ በመጨረሻ የተናገራቸው ቃላት ።

ይህ የመጽሐፈ ኢያሱ የመጨረሻ ክፍል ነው ። የሚያመለክተውም ኢያሱ በጣም አርጅቶ ፣ ወደ ሞትም ተቃርቦ የነበረበትን ጊዜ ነው ። በዚህ ወቅት እስራኤላውያን በዙሪያቸው በነበሩ ጠላቶቻቸው ላይ ሁሉ ድልን አግኝተው ነበር ። እግዚአብሔር ከርስታቸው ጋር ሰላምንና ዕረፍትን ሰጥቶአቸው ነበር ።

ኢያሱ በዕድሜው በጣም በማርጀቱ በምድር ላይ የቀረው በጣም አጭር የሆነ ጊዜ መሆኑን ስለተረዳ የእስራኤል አለቆችን በሙሉ ወደ እርሱ ሰበሰበና የመጨረሻ ምክርና መልእክት ሊሰጣቸው ጀመረ ።

ለእነዚህ ሰዎች ባደረገውም የመጨረሻ ንግግር እግዚአብሔር ዮርዳኖስን ከመሻገራቸው አንስቶ ርስት እስከመከፋፈላቸው ያደረገላቸውን አስታወሳቸው ፤ 23፡3-5 ። ስለዚህም እርሱን መታዘዝና ከሌሎቹ አሕዛብም ጋር መቀየጥ የማይገባቸው መሆን አሳሰባቸው ፤ 23፡6-7 ። ይህንን የእግዚአብሔር ትእዛዝ በመተላለፍ በምድሪቱ ይኖሩ ከነበሩት አሕዛብ ጋር ቢደባለቁ ግን ወደፊት ምንም ዓይነት ድል ማግኘት እንደማይችሉ ገለጸላቸው ፣ 23 ፡13 ። እንዲያውም ከመተላለፋቸው የተነሣ የሚያጠፋቸው መሆኑን አስጠነቀቃቸው ፤ 23፡14-16 ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ትእዛዞች ለአዲስ ኪዳን

አማኞችም የሚጠቅሙ ናቸው ። ዛሬም ቢሆን ጌታ ክርስቲያ ኖች ከዓለም እንዲለዩ ያዛል ፣ 2 ቆሮ. 6፡14-18 ። እግዚአብሔ ርንና ዓለምን በአንድ ጊዜ መውደድ የሚችል ማንም የለም ። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው በሙሉ ፍቅር እንድንወደው ነው ፤ 1 ዮሐ. 2፡15 ።

በመጨረሻም ኢያሱ የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ ወደ ሴኬም ሰብስቦ ምክር መስጠቱ በምዕራፍ ሃያ አራት ውስጥ ተገልጿል ። እግዚአብሔር አብርሃምን ከጠራበት አንስቶ የተስ ፋዪቱን ምድር እስከያዙበት ጊዜ ያገኟቸውን በረከቶች በሙሉ ነገራቸው ። በዚሁም ወቅት እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸ ውን አሥራ ስድስት ታላላቅ ነገሮች ተረከላቸው ፤ 24፡3-13 ። ስለዚህ እስራኤላውያን አምላካቸውን እግዚአብሔርን ሊያገለ ግሉት ይገባቸዋል ። እርሱን ለማገልገል እምቢተኛ መሆን የአ ብርሃም አባት ፣ ወይም የከነዓን ምድር ሰዎች ሲያመልኳቸው የነበሩትን ጣዖታት ማምለክ ነው ።

ኢያሱ በዚሁ ጉባዔ ላይ የራሱን እምነት ገለጸ ። እርሱና በእርሱ ቤተሰብ የሚኖሩት እግዚአብሔርን ለማምለክ መርጠ ዋል ፤ 24፡14-15 ። ሕዝቡም እግዚአብሔርን በማምለክ የሚ ጸኑ መሆናቸውን በግልጽ ተናገሩ ፤ 24፡16-18 ።

በንግግሩም ማጠቃለያ ኢያሱ እግዚአብሔር ቅዱስ አም ላክ ስለሆነ ኃጢአት ቢሠሩ በይቅርታ ብቻ የማያልፋቸው መ ሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው ። ሕዝቡም በእርግጥ እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው ለማገልገል ቃል ገቡ ፤ 24፡19-21 ። በመሃከላቸው ያሉትን የተለያዩ አማልክት ለማስወገድ ተስማሙ ፤ 24፡22-24 ።

ከዚህ በኋላ ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ። ይህ

ንንም ኪዳን በመጽሐፍ ጽፎ በሙሴ ሕግ ግለትም ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ባለው መጽሐፍ ላይ ጨመረው ። በመጨረሻም ለመጪው የእስራኤል ትውልድ ምስክር እንዲሆን በሴኬም በአንድ ዛፍ ሥር አንድ ትልቅ ድንጋይ አቆመ ፤ 24፡25-28 ።

ይህ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ እስራኤላውያን ይኖሩ የነበረው በድንኳን ውስጥ ነበር ፤ 3፡14 ። ከዚህ በኋላ ግን ነገዶቹ በሙሉ ርስታቸውን ስለአገኙና ጦርነቱ ስለአበቃ ሁሉም ወደየርስቱ ተመለሰ ፤ 24፡28 ።

ኢያሱ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲከተሉ የተቻለውን ያህል ጥረት ያደረገ መሪ ነው ። የሕይወት ዘመኑንና ዕድሜውን በሙሉ የጨረሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆን ነበር ። ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሥራ በሙሉ አጠናቀቀ ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ርስታቸውን ለመያዝ ፣ በዕረፍት በምድራቸው ለመቀመጥ አበቃቸው ። የዚህ መጽሐፍ መደምደሚያ የሆኑት የመጨረሻዎቹ አምስት ቁጥሮች ኢያሱ ዕድሜው መቶ አሥር እንደሞላና በዚሁ ዕድሜው እንደሞተ ይነግሩናል ። በምድር ላይ የኖረበት ዕድሜ ርዝመት ከሞላ ጐደል ከሙሴ ዕድሜ እኩል ነው ።

ኢያሱ ከሞተበት ጊዜ በኋላ ያለውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ስንመለከት ሁኔታቸው እንደተለወጠ እንረዳለን ። ሕዝቡ እግዚአብሔር የሠራውን የሚያውቁ ሽማግሌዎች በነበሩበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን አመለኩ ። መጽሐፉ የሚደመድመው ኢያሱ ሞቶ መቃብሩን ፣ ከዚያም እስራኤላውያን ከግብጽ ያወጡትን የዮሴፍን አጽም መቅበራቸውን የአሮንም ልጅ ሞቶ መቀበሩን በመግለጽ ነው ፤ ዘፍጥ. 50፡25 ፤ ዘጸአት 13፡19 ።

ኢያሱ በሕይወቱ ዘመን መጨረሻ ላይ የተናገራቸው ቃላት ለክርስቲያኖች ጥልቅ የሆነ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው ። ክርስቲያኖችም ደኅንነታቸውን ተገን አድርገው ኃጢአት መሥራት የሌለባቸው መሆኑን ያስተምራሉ ። እስራኤላውያን ከውጊያ ሁሉ አርፈው በሰላም በምድራቸው መቀመጣቸው ክርስቲያኖችም አንድ ቀን ከዓለም ሩጫ ተገላግለው በእግዚአብሔር ፊት በዕረፍት በሰላም የሚኖሩበት ዘመን የሚመጣላቸው የመሆኑ ምሳሌ ነው ።

እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔርን በመታመን ያገለገለው ኢያሱ ለአብያተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ ለምዕመናን በአጠቃላይም ለአገልጋዮች መልካም አርአያ የሆነ መሪ ነው ።

እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን የሚለው የኢያሱ ንግግር ዛሬም ክርስቲያን የሆኑ የቤተ ሰብ መሪዎች በተለይም አባቶች ሊከተሉት የሚገባ መመሪያ ነው ።

ኢያሱና አልዓዛር ሁለቱም የጌታ ኢየሱስ ምሳሌዎች ናቸው ። ኢያሱ የሚለው ስም በአዲስ ኪዳን ለክርስቶስ ከተሰጠው ኢየሱስ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ የሆነ አዳኝ የሚል ትርጉም አለው ። ጌታችን ኢየሱስ የእኛ ሊቀ ካህን ፣ የእኛ አልዓዛር ነው ። ቢሆንም ኢያሱና አልዓዛር በመቃብር ተወስነው ቀርተዋል ። የእኛ አዳኝና ሊቀ ካህን የሆነው ኢየሱስ ግን በመቃብር አልተገታም ፣ ሞትን አሸንፏል ፣ ለዘለዓለምም ሕያው ነው ። እርሱ ለኃጢአታችን በመሞት ከኃጢአት ዕዳ ነፃ አውጥቶናል ። ሊቀ ካህናችንም በመሆኑ በአባቱ ቀኝ ሆኖ ይማልድልናል ። በየዕለቱም በኃጢአትና በሰይጣን ላይ ድልን ይሰጠናል ። በመጨረሻም ኢያሱ እስራኤላውያንን ከተስፋው ምድር መርቶ እንደአደረሳቸው እኛንም በዕረፍት ወደምንኖርባት ሀገራችን ይወስደናል ፤ ከዚያም ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንኖራለን ።

ክፍል ስድስት

ማጠቃለያ

ከመጽሐፈ - ኢያሱ የምናገኛቸው ትምህርቶች ።

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚሰጠው ትምህርት

መጽሐፈ ኢያሱ በእርግጥ ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት የሚገኝበት መጽሐፍ ነው ። እግዚአብሔር ኢያሱን እንደ ተናገረው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተነግሯል ፣ በተጨማሪም እግዚአብሔር ሙሴን የተናገረው መሆኑም ሰባት ጊዜ ተጠቅሶአል ፤ ለምሳሌ 1፡3 ፤ 11፡15 ። እግዚአብሔር ሙሴን የተናገረው መሆኑን እስራኤላውያን እራሳቸው ያምናሉ ። እንዲሁም እግዚአብሔር ለኢያሱ ይናገራል የሚል እምነት ስለነበራቸው እስራኤላውያን ወደ ኢያሱ እየቀረቡ ጥያቄዎችን ይጠይቁት ነበር ፤ ለምሳሌ ያህል ካሌብ ፣ 14፡9፤ የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች፣17፡3-4፤ ሌዋ. 21 ፣ 1-2 ። እነዚህም ጥቅሶች በሙሴ የተጻፉት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር አሳብ የወጡ መሆናቸውን ያስተምሩናል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ መሆናቸው በ2 ጢሞ. 3፡16 ተነግሯል ።

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚሰጠው ትምህርት

1. **እግዚአብሔር ኃያል ነው ፡-** ሕዝቦቹ ከጠላቶቻቸው ጋር ያደርጉት በነበረው ውጊያ ላይ ሊረዳቸው ከሰማይ የበረዶ

ድንጋይን በጠላቶቻቸው ላይ ያወረደ አምላክ ነው ። እን ዲሁም ሕዝቡ ድል እስኪያገኙ ድረስ ፀሐይ ከመዋለቅ እንድትዘገይ ያደረገ ጌታ ነው ፤ ኢያሱ 10፡11-13 ።

2. <u>ሁሉን የሚያውቅ ነው</u> ፡- አካን ኃጢአቱን ከእግዚአብ ሔር ሊሰውር አልቻለም ፣ 7፡ 1 ። የሮቤል ፣ የጋድና የምናሴ ነገዶች ሰዎች እግዚአብሔር እነርሱ ሌላ መሥዋ ዕት የሠሩበትን ምክንያት ያወቀ ለመሆኑ እርግጠኞች ነበሩ ፤ ኢያሱ 22፡22 ።

3. <u>ቅዱስ ነው</u> ፡- ሕዝቡ ዮርዳኖስን ለመ፟ገር ጉዞአቸውን በቀጠሉበት ወቅት በእነርሱና በእግዚአብሔር ታቦት መሃከል መጠነኛ ርቀት መኖር ነበረበት ። ኢያሱም ራሳ ቸውን እንዲቀድሱ ተናግሮአቸው ፣ ዘዳር ፣ 3፡ 4-5 ። ዮርዳ ኖስንም ከተሻገሩ በኋላ በሕጉ መሠረት የግዘረትን ሥር ዓት እስኪፈጽሙ ድረስ በረከትንም ሆነ ድልን አልሰጣ ቸውም ፤ 5፡5። እግዚአብሔር እስራኤላውያን በአካን ኃጢአት ላይ እስከፈረዱበት ጊዜ ድረስ ድል አለመስ ጠቱ እራሱ ቅድስናውን የሚያሳይ ነው ፤ 7፡1። ኢያሱም እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ መሆኑን ተረድቷል ፣ 24፡19 ።

4. <u>ጻድቅ ነው</u> ፡- እግዚአብሔር የከነዓን ሰዎች ታላቅ ኃጢ አት ያደረጉ ክፉ ሰዎች ሆነው ስለአገኛቸው የእስራኤል ሰዎች እንዲያጠፉአቸው ትእዛዝ ሰጠ ። የከነዓን ሰዎች ም ከእስራኤል ሰዎች ጋር እንዲዋጉ እግዚአብሔር ልባ ቸውን አጠነከረ ፤ 11፡20 ። በሰንም የተባለው እግዚአብ ሔርን በከፊል የታዘዘው ነቢይ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ጋር ጠፋ ፤ 13፡22 ።

5. መሐሪ ነው፡-ለእስራኤል ጠላት ለነበሩት ሕዝብ ትክክለኛ ጽድቁን ፥ ለእውነተኛ ሕዝቦቹ ደግሞ ምሕረቱን በመደጋገም አሳይቷል ። ለእስራኤል ሰዎችም ተዋግቷል ፤ 10፡12 ።

6. ታማኝ ነው ፡- ከኢያሱ ጋር ለመሆን የሰጠውን የተስፋ ቃሉን እስከ መጨረሻው ጠብቋል ፤ 1፡5፤ 24፡18። እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡበት ጊዜ አንስቶ ተስፋዪቱ ምድር እደረሱበት ጊዜ ድረስ በታማኝነቱ መናን መግቧቸዋል ፤ 5፡12 ። ስለዚህም ኢያሱ እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ ፈጸሚ መሆኑን ተምሮአል ፤ ተለማምዷልም ፥ 21፡45 ፤ 33፡14 ።

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረው ትምህርት

እግዚአብሔርን ያየ ማንም እንደሌለ ሁላችንም እናውቃለን ። እግዚአብሔርን እንድናውቀው ስለ እግዚአብሔር የገለጸልን ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ዮሐ. 1፡18 ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፤ መጀመሪያ የሌለው አምላክ ነው ።

እግዚአብሔር ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበረው የብሉይ ኪዳን ዘመን አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እርሱን እንዲያዩት ያደርግ ነበር ። ቢሆንም ከዮሐ. 1፡18 መረዳት እንደሚቻለው ከሆነ ያን ጊዜም ቢሆን ሰዎች የተመለከቱት ራሱን ጌታ ኢየሱስን ነበር ። የኢያሪኮ ከተማ ግንብ ከመውደቁ በፊት ጌታ አንድ የሠራዊት አለቃ ሆኖ ወደ ኢያሱ በመምጣት ፥ ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ነገረው ፤ ኢያሱ 5፡15 ።

ክርስቶስ ለሰዎች ኃጢአት በመስቀል በሞተበት ጊዜ የሰ

ዎች ሁሉ አዳኝ ሆነ ። ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋ ንቋ ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ነው ። ኢያሱ የሚለ ው የዕብራይስጥ ቃልና ኢየሱስ የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉማ ቸው ተመሳሳይ ነው ። ኢየሱስ ማለትም አዳኝ ማለት ነው ፥ ማቴ 1፡21 ።

ኢያሱ የኢየሱስ ምሳሌ ነው ፤ ኢያሱ እግዚአብሔርን የታ ዘዘ ሰው ነው ፤ ኢየሱስ ግን ያለ ነቀፋ ሙሉ በሙሉ እግዚአብ ሔርን ታዘዘ ። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ደኅንነ ትና ወደ ድል አድራጊነት መርተዋል ። ኢያሱና የእስራኤል ል ጆች ብዙ ጠላቶች ነበሩዋቸው ። እግዚአብሔር ግን በኢያሱ በኩል ድል ሰጣቸው ፤ አማኞችም እንዲሁ ናቸው ፤ እግዚአብ ሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል አድራጊነትን ይሰጣ ቸዋል ፥ 1ቆሮ. 15፡57 ፤ 2 ቆሮ. 2፡14 ። መጽሐፈ ኢያሱ በአን ዳንድ መንገዶች ከኤፌሶን መልእክት ጋር ይመሳሰላል ። በሁለ ቱም መጻሕፍት ውስጥ ከጠላት ጋር የሚደረገው ውጊያ ተገል ጿል ፤ በሁለቱም መጻሕፍተ ውስጥ በአዳኛችን በኢየሱስ በኩል የሚገኘው ታላቅ በረከት ተነግሯል ፥ ኤፌ. 6፥ 12፤ 1፥ 3 ። ማንኛ ውም መልካም ነገር የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው ።

መጽሐፈ-ኢያሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት

መጽሐፈ-ኢያሱ ስለ መንፈስ ቅዱስም ሆነ መናፍስት ስለ ሆኑት መላእክት ምንም የሚገልጸው ነገር የለም ። እነዚህን የሚመለከቱ ትምህርቶች በሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግግኘት ይቻላል ።

መጽሐፈ-ኢያሱ ስለ ሰው የሚሰጠው ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰውና ስለ ኃጢአት በሰፊው ያስተምራል ፣ በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ የሚገኘው የአካን ታሪክ ስለ ሰው ኃጢአት አብራርተው ከሚያስተምሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ ነው ። ይህ ታሪክ እያንዳንዱ ሰው ጌታን ለመከተል የራሱ ምርጫ እንዳለውና እንደሚያስፈልገው ያስተምረናል ፣ ኢያሱ 24 ፡ 15 ።

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ ደኅንነት የሚያስተምረው ትምህርት

አማኞች በክርስቶስ ያገኙት ደኅንነት በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ በሥዕላዊ ሁኔታ ተገልጿል ። የእስራኤል ሕዝብ ለንጉሥ ለፈርዖን ባሪያዎች እንደነበሩ ሁሉ ክርስቲያኖችም የሰይጣንና የኃጢአት ባሪያዎች ነበሩ ። የፋሲካው ጠቦት ደም ከሞት መቅሠፍት አዳናቸው ፤ የእግዚአብሔርም ኃይል ባሪያዎች ሆነው ከሚኖሩበት ከግብፅ ምድር አወጣቸው ፤ ቢሆንም የዮርዳኖስን ወንዝ እስከተሻገሩበት ጊዜ ድረስ ወደ ተስፋዪቱ ምድር አልገቡም ። የዮርዳኖስ ወንዝ የሞት ምሳሌ ነው ። እኛም አማኞች ለኃጢአት እስካልሞትን ድረስ ከጌታ የተሰጠንን በረከት ልንደሰትበት አንችልም ፤ ሮሜ 6፡11 ። ከጌታ ከኢየሱስ ጋር በመስቀል ላይ ሞተናል ፤ ገላ. 2፡20 ።

እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ እንደተሻገሩ እኛም ፡ ከሞት ወደ አዲስ ሕይወት ፡ ከመርገም ወደ በረከት ተሻግረናል በምዕራፍ 20 ውስጥ የተገለጹት የመማጸኛ ከተሞች የጌታ ኢየሱስ ምሳሌ ናቸው ፤ ኃጢአተኛ ወደ ክርስቶስ ሸሽቶ በመጠጋት ሕይወትን ያገኛል ።

መጽሐፈ-ኢያሱ ስለ እምነት የሚያስተምረው ትምህርት

በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ስለ እምነት የሚያስተምሩ አስደናቂ ምሳሌዎችን እናገኛለን ። ጋለሞታዪቱ ረዓብ እግዚአብሔር የኢያሪኮን ከተማ ለእስራኤላውያን አሳልፎ መስጠቱን አምና ነበር ። ምኞቷም የእርሷና የቤተሰቧ መዳን ነበር ፤ 2፡9፣12 ። ካሌብ ለብዙ ዓመታት የእግዚአብሔርን ተስፋ በእምነት ይጠባበቅ የነበረ ሰው ነው ፤ በእርጅናው ዘመን በዚሁ እምነቱ በመጽናት ጠላቶቹን በጦርነት ገጥሞ ድል አደረጋቸው ፤ 14፡6-13 ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ድል በመስጠት እንዲታመኑበት የሚያደፋፍራቸው መሆኑንም ከዚሁ መጽሐፍ እንመለከታለን ። ለምሳሌ ኢያሱ ለስለላ ወደ ኢያሪኮ ከተማ መውጣቱ እምነቱን አጠነከረለት ፤ 2፡24 ።

ጌታም ራሱ የኢያሱን እምነት ለማጠንከር የተለየ መልእክት ሰጠው ፥ 11፡6 ። የሚቀጥለው የእስራኤል ትውልድ እንዲመለከታቸውና በእነርሱም አማካይነት የእግዚአብሔርን ታላቅነት አውቆ እንዲታመንበት ለማድረግ እግዚአብሔር ለኢያሱ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን እንዲተክል አዘዘው ፤ 4፡6፣21 ። ኢያሱ እምነቱን ባሳየበት ወቅት ጌታ ለሕዝቦቹ አስደናቂ ተአምር አድርጓል ፤ 10፡12-13 ።

በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤል ልጆች በራሳቸው ጥበብ በሚሄዱበት ወቅት ለሚፈጽሙት በደል በሚገጥማቸው ችግር ና ሥቃይ ዋጋ መክፈል ነበረባቸው ፥ 9 ፣ 14 ፣ 18 ። እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን በማይታዘዙ አማኞች ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጽማል ፤ ታማኝ የሆኑት ልጆቹ የሚያቀርቡለትን የእምነት ጸሎት በድል ሲመልስ፤ የማይታዘዙትን ደግሞ ይቀጣቸዋል ።

በእግዚአብሔር የምንታመን ከሆንን እርሱን መታዘዝ ያስፈልገናል ። በ1፡8 እግዚአብሔር ለኢያሱ ሕጉን እንዲታዘዝ ሲያስጠነቅቀው እንመለከታለን ። የኢያሱንም ታሪክ ስንመለከት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ጌታን እንደታዘዘ እናያለን ። ለምሳሌ የኢያሪኮን ከተማ ለመያዝ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ፈጽሞአል ፤ 6፡11፤20፤11፡9 ። ሌሎችም እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ (23፡ 6) እንዲሁም እንዲያፈቅሩት (22፡5፤23፡11) ተናግሮአል ። ኢያሱም ሆነ የእስራኤል ሕዝብ የሙሴን ሕግ እንደጌታ ትእዛዝ አድርገው በመቁጠር ታዘዙ ፤ 8፡29-35 ፤ 10፡26 ።

በ1፡16 ውስጥ የሮቤል ፥ የጋድና የምናሴ ነገድ ሰዎች ሁላችን ልንከተለው የሚያስፈልግ በጣም ጥሩ የሆነ ቃል እንደተናገሩ እንመለከታለን ። በተናገሩትም ቃል የሰጡትን ተስፋ ፈጸሙ ፤ ቢሆንም ጌታ ያላዘዛቸውን ሌሎች ድርጊቶችንም ፈጸሙ ፥ 22፡10 ። እግዚአብሔርን ብንታዘዝ እርሱም ድልን ይሰጠናል ። የኢያሱም መጽሐፍ ስለ ብዙ ድሎች ይተርክልናል ። የእስራኤል ልጆች ከኢያሪኮ በስተ ምዕራብ በጋይ (ምዕ.8) በደቡብ በኩል (10፡40-42) በሰሜን በኩል (11፡23) ድሎችን ቢጐናጸፉም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንዳንድ በኩል ውድቀት እንደነበረባቸው እናያለን ፤ 15፡63፤16፡10 ።

እግዚአብሔር በጠቅላላው ምድሪቱን ሰጣቸው ፤ መውረስ የቻሉት ግን ተዋግተው ያስለቀቁትን አካባቢ ብቻ ነበር ። ይህም በክርስቶስ ስለምናገኘው በረከት ጥልቅ የሆነ ትምህርት ይሰጠናል ። እግዚአብሔር ለእኛም ብዙ ስጦታዎችን ሰጥቶአል ስጦታዎቹን በእጃችን ውስጥ ማስገባት የምንችለው በእምነት ውጊያችንን ወደፊት ስንቀጥልና ጠላቶቻችንን ድል ስናደርግ

ነው ። መጽሐፈ ኢያሱ ውጊያ ሳያደርጉና ሳይሠሩ ሁሉን ነገር ማግኘት ስለሚፈልጉ ሰዎችም ጥሩ ትምህርት ይሰጠናል ። ለም ሳሌ የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች ሰዎች ርስታችን ጠበበን የሚል አቤቱታ አቅርበው ነበር ፤ 17፡14። ሌሎቹ ነገዶች ደግሞ ርስታቸውን ከመውሰድ ወደኋላ ዘግይተው ነበር ።18፡3 ። እነዚህ ሁሉ በእምነት መበርታት ያለብን መሆኑን የሚያስተምሩን ናቸው ።

መጽሐፈ-ኢያሱ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚያስተምረው ትምህርት

የቤተ ክርስቲያን እውነትና ምሥጢር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጽ አይታይም ፤ ምሥጢሩ ጉልህና ግልጽ ሆኖ የሚ ታየው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው ፤ ኤፌ. 3፡5። መጽሐፈ ኢያሱ ስለቤተ ክርስቲያን ጥቂት ሥዕላዊ መግለጫዎችን ይሰ ጣል ። የእስራኤል ሕዝብ የፋሲካን በዓል ያከብሩ ነበር ፤ 5፡10። ይህ በዓል የሚያመለክተው ወደፊት ስለሚፈጸመው የጌታ ኢየሱስ ሞት ነው ። ይህ በዓል ወደፊት ስለሚሆነው ያመለክት እንደነበረ ሁሉ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ዘመን ያሉ አማ ኞች በአንድነት ተሰብስበን የጌታን እራት ጎብስተ በመቁረስ የፋሲካ በዓል ምሳሌው የነበረውን የጌታን ሞት መለስ ብለን እናሰላስላለን ፤ 1 ቆሮ. 11፡23-26 ። እግዚአብሔርን ማምለክ ችን እንደ ካህናት ማገልገላችን ነው ፣ 1ጴጥ. 2፡5። ክህነት ተሰ ጥቷቸው የነበሩት የሌዊ ልጆች እንደ ሌሎቹ ርስት እንዳልተሰ ጣቸውና የእነርሱ ርስት ክህነታቸው እንደነበረ ከመጽሐፈ ኢያሱ ተመልክተናል ፤ 13፡33 ፤ 18፡7 ። ለእነዚህ ካህናት የሚኖ ሩባቸው ከተሞች ግን ተሰጥተዋቸው እንደነበረም አይተናል ።

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጣቸውን መምሪያ ትተው የራሳቸውን ጥበብ በመከተል የተለያዩ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ ። በሮቤል ፣ በጋድና በምናሴ ነገዶች የተሠራው መሠዊያ ሁኔታ ለነዚህ አገልጋዮች ጥሩ ትምህርት ይሰጣል ፤ 22፡10። እነርሱ ሠርተውት የነበረው መሠዊያ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ በሩቅ ሊታይ የሚችል ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሠራ አልነበረም ።

መጽሐፈ -ኢያሱ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚሰጠው ትምህርት

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ መጨረሻው ዘመን ምንም ትምህርት አይሰጥም ፤ አንዳንድ ጊዜ ግን የከነዓን ምድር የመንግሥተ ሰማይ ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል ። ጌታችን ተመልሶ ሲመጣ በጠላቶቹ ላይ የሚነግሥ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ቢሆንም እኛን አማኞችን ዛሬም ቢሆን ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ አስቀምጦናል ፤ ኤፌ 2፡6። ከዚህ አንጻር ሲታይ በአሁኑ ወቅት እኛ አማኞች የታላቅ በረከት ተከፋዮች ነን ማለት ነው ፤ ቢሆንም ብዙ የምንዋጋቸው መንፈሳዊ ጦርነቶች መኖራቸውን መዘንጋት የለብንም ፤ ኤፌ. 6፡12 ። በመንግሥተ ሰማይ መኖር ስንጀምር ግን እነዚህ ጦርነቶች ያከትማሉ ።

ስለዚህ ነው የከነዓን ምድር አማኞች በጌታ በኢየሱስ ሆነው በዚህ ዓለም ላይ የሚያገኙት ድል ምሳሌ ተደርጎ የተሠራበት ፤ ይህም አዳኛችን ለሆነው ለእውነተኛው ኢያሱ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን ይሰጣል ።

ለዚህ ታላቅ ድል የሚያበቃን ታማኙና ኃያሉ አምላካችን ከእውነተኛ ተከታዮቹ ሁሉ ክብርና ምስጋና ይድረሰው ! አሜን ።

ሁሴን የሱፍ

የመጽሐፍ ቅዱስ ት ቤት አስተባባሪ ።